# የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ

የዚህ ጽሑፍ አላማ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ግምት ውስጥ በማስገባት እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን በተመለከተ ለባለድርሻና አጋር አካላት አጫጭር ወቅታዊ መረጃዎችን ማድረስ ነው፡፡

## የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የግብርና የኤክስቴንሽን ኮሙዩኒኬሽን መመሪያ ተዘጋጀ

የግብርና ሚኒስቴር የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝን በመከላከል የግብርና ስራዎችን በወቅቱና በተገቢው መንገድ ለማከናዎን ይቻል ዘንድ የግብርና ኤክስቴንሽን ኮሙዩኒኬሽን መመሪያ አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት አሰራጭቷል፡፡

ከዚህ በፊት በስፋት ይሰራባቸው የነበሩ እንደ ስልጠና፣ ስብሰባ፣ የቡደንና የአቻላቻ ውይይቶች አርሶ አደሮችና ባለሙያዎች ተቀራርበው በመነጋገርና ሃሳብን በመለዋወጥ ይጠቀሙባቸው የነበሩ የኤክስቴንሽን ዘዴዎች በዚህ ወቅት ከኮሮና ቫይረስ ስርጭት አመችነት አንጻር የሚያስሄዱ ሆነው አልተገኙም፡፡ በዚህም ምክንያት በዚህ ዓመት ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ በተዋረድ ሊሰጡ የታቀዱ በርካታ ስልጠናዎችና ስብሰባዎች እንዲሰረዙ ተደርጓል፡፡ ይህ ማለት ግን የኤክስቴንሽን ኮሙዩኒኬሽን ድጋፍ አይደረግም ማለት አይደለም፡፡ የግብርና ባለሙያወች እራሳቸውንና አርሶአደሮችን ከኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በመጠበቅና የተለያዩ አማራጭ ዘዴዎችን በመጠቀም ድጋፋቸውን ይቀጥላሉ::

የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚሰጡ የግብርና ኤክስቴንሽን ዘዴዎች ከወቅቱ አንጻር ተመራጭ መንገዶች ናቸው:: በዚህ መንገድ ለምሳሌ ስለወቅታዊ የአየር ትንበያ መረጃ፣ የተባይ እና የበሽታ ክስተት፣ የቀን ሰራተኛ ፍላጎት እና መሰል መልዕክቶችን ማስተላለፍ ይቻላል::

አሁን ካለው ወቅታዊ ችግር አንጻር መንግስት በትኩረት ሊሰራባቸው የሚገቡ የኮሙዩኒኬሽን ዘዴዎችን ለይቶ አስቀምጧል፡፡ ከግብርና ሚኒስቴር በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት በዘንድሮው የምርት ዘመን በስፋት የኤክስቴንሽን ኮሙዩኔኬሽን አገልግሎት የሚሰጠጥባቸው ዋናዋና የኮሙዩኔኬሽን ዘዲዎች;- 8028 ነፃ የስልክ ጥሪ፣ በየክልሉ የሚገኙ የሬድዩ ጣቢያዎች (አሳታፊ የሬድዩ ፕሮግራሞች)፣ ቴሌቪዝን፣ የድምጽ ማጉያ፣ እንደ ፖስተርና በራሪ ጽሑፎችን የመሳሰሉ የህትመት ውጤቶች፣ ኢ-ሜይልና ለቴሌ ኮንፈረንስ የሚያገለግሉ የኢንተርኔት መተግበሪያዎች ናቸው::







## ከኮኖና ቫይረስ ወረርሽኝ እራስዎን ይከላከሉ!




እጅዎን በንጽህ ውሃና በሳሙና ይታጠቡ ወይም አልኮል ባለው የጀርም ማጽጃ ያጽዱ



እጅዎን ሳይታጠቡ አፍዎን፣ አፋንጫዎንና አይንዎን አይንኩ



በእጅ መጨባበጥን ያቁሙ




ከሰዎች ጋር የሚኖርዎትን አካላዊ ርቀት ይጠብቁ

ከነዚህ በተጨማሪም መንግስትና የጤና ባለሙዎች የሚሰጧቸውን ሌሎች መመሪያዎች ይከተሉ!

# የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ 19) ወረርሽኝን ከግምት ውስጥ ያስገቡ የግብርና ልማት ስራዎች እየተካሄዱ ነው



የኮሮና ቫይረስ ክስተት የብዙዎችን ሕይወት እቀጠፈና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስን እያስከተለ ይገኛል፡፡ ሃገራትና መንግስታት የቫይረሱን ስርጭት ለመግታትና በቫይረሱ የተጠቁ ሰዎችን ሕይወት ለመታደግ የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰዱ ይገኛሉ፡፡ ቫይረሱን ለመከላከል እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች የሰዎችን ሕይወት ከመታደግ አንፃር ውጤት እያስገኙ ቢሆንም በአንፃሩ በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን እያደረሱ ይገኛሉ፡፡ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች በተለይ እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮችን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ኢኮኖሚያቸውን የበለጠ እያዳከሙት ይገኛሉ፡፡ በቫይረሱ ምክንያት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እስከ 11% እንደሚቀንስ እየተነገረ ይገኛል፡፡

## የቫይሱ ስርጭት በግብርና ልማት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ

ከቫይረሱ ስርጭት ጋር በተየያዘ የብዙዎች ስጋት ሁኔታዎች በግብርና ልማትና በምግብ አቅርቦት ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት አሉታዊ ተፅዕኖ ነው፡፡ የምግብና የእርሻ ድርጅት (ፋኦ) የቫይረሱ ስርጭት፣ በዚህ ምክንያት የሰራተኞች እንቅስቃሴ የተገደበ መሆን፣ አስፈላጊ የእርሻ ግባዓቶች ስርጭት መስተጓጎል በምግብ ምርትና ተደራሽነት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖና ጫና እንደሚያስከትል ገልጿል፡፡

በኢትዮጵያ የክረምቱ ወራት ገና ቢሆንም የቫይረሱን ስርጭት ከወዲሁ መቆጣጠረ ካልተቻለ የ2012/13 የምርት ዘመን የግብርና ልማት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ በማድረስ ምርትና ምርታማነትን ሊቀንስ ይችላል፡፡ በዚህም በሚቀጥለው ዓመት የምግብ እጥረት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ይህንን በሚመለከት የግብርና ሚኒስቴር በሚቀጥለው የምርት ዘመን እስከ 8% ወይም እስከ 40 ሚሊዮን ኩንታል የሚደርስ የምርት ቅናሽ ሊኖር እንደሚችል ግምቱን አስቀምጧል፡፡

## ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች

ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መንግስት በግብርና ሚኒስቴርና በተዋረድ በየክልሉ የሚገኙ የግብርና ቢሮዎች እንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ ሌሎች ባለድርሻና አጋር አካላት በቫይረሱ ምክንያት ሊደርሱ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን በመቀነስ የምርት ዘመኑን በተሻለ ሁኔታ ለማስኬድ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በሰሊጥ መረብ ውስጥ ለሚገኙ አርሶ አደሮች ድጋፍ የሚያደርጉ የአማራና ትግራይ ክልል ግብርና ቢሮዎችም በተዋረድ እስከ ቀበሌ ድረስ በተዘረጉ መዋቅራቸው እንዲሁም የግብርና ምርምር ኢንስቲትዮቶች እና ማዕከላት በተለይ ከእርሻ ስራ ወቅት በፊት ሊከናወኑ የሚገባቸውን ዋና ዋና ስራዎች ለምሳሌ የምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ እና ሌሎች ግባዓቶችን አቅርቦትና ስርጭት በታቀደውና በተጠበቀው መልኩ እንዲፈጸሙ፤ እንደ ማሳ ዝግጅት፣ ክላስተር አደረጃጀት የመሳሰሉ ሌሎች መሰል ቅድመ ምርት ዝግጅቶችን በተገቢው መንገድ ለማከናወን እየተጉ ይገኛሉ፡፡

## የቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን ድጋፎች

ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች መሰል ጥረቶችን ለመደገፍና የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ የድጋፍ ፕሮግራም (ቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን) አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ይገኛል፡፡

የኮሮና ቫይረስን ስርጭት ለመግታት ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ሂደትን መቀነስና እንዲሆም ቤት ውስጥ መቀመጥ እንደዋና መፍትሔ በተወሰደበት ሁኔታ ከወረዳ ወደ ዞን ብሎም ወደክልል የሚደረጉ ግንኙነቶችን/ውይይቶችን ለማሳለጥ ዘመናዊ የኢንተርኔት ቴክኖሎጅ መተግበሪያዎችን መጠቀም አይነተኛ አማራጭ መንገድ ነው፡፡ በተለይ ሦስትና ከዛ በላይ ሰዎችን ለማገናኘትና ለማወያየት የኢንተርኔት መተግበሪያዎች በተለያዮ ቦታዎች ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡ እንደ ዙም (zoom) ያሉና ወቅቱን የዋጁ አይነተኛ መተግበሪያዎች የኢንተርኔት አገልግሎት ተደራሽ በሆነባቸው አካባቢዎች ውይይቶችን ለማካሄድና በፍጥነት መረጃ ለመለዋወጥ ከፍተኛ እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

ቤኔፊት ኤስ ቢ ኤን ባደረገው ዳሰሳ መሰረት መሬት ላይ ያለውን የግብርና ልማት እንቅስቃሴ እያመቻቹ የሚገኙ በርካታ የወረዳ ግብርና ጽህፈት ቤቶች የኢንተርኔት ተጠቃሚ አይደሉም፡፡ ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በ12 የሰሜን ምዕራብ ቆላማ ወረዳዎች የሚገኙ የግብርና ጽህፈት ቤቶችንና አምስት ዮኒዮኖችን የኢንተርኔት ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት እያደረገ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በዚህ በኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ አስከፊ ጊዜ በተለይ ሬድዮን በመጠቀም ወቅቱን የጠበቀና በባለሙያ የተደገፈ መመሪያና የመረጃ አገልግሎት በመስጠት አርሶ አደሮችና የግብርና ባለሙያዎች ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ስራቸውን እንዲሰሩ፤ በተለይ አርሶ አደሮች የተሻሻለ የአሰራር ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ ለማድረግ እየተከናወኑ ያሉ ስራዎችን ለመደገፍ ጥረት ያደርጋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የምርጥ ዘር ስርጭትን በተመለከተ የፍላጎት ዳሰሳ አካሂዷል፡፡ ስርጭቱንም ለማገዝ ከጎንደርና ሁመራ የግብርና ምርምር ማዕከላት እንዲሆም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር እየሰራ ይገኛል፡፡ የአየር ፀባይ ትንበያን ለአርሶ አደሮች ተደራሽ ለማድረግ የሚደረጉ ጥረቶችን በመደገፍ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ሜትየሮሎጅ ኤጀንሲና ዌዘር ኢምፓክት ከተሰኘ ፕሮጀክት ጋር በመተባበር በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ለሚገኙና 9000 ለሚሆኑ አርሶአደሮችና ባለሙያዎች በመጭው የምርት ጊዜ

## በሰሊጥ ልማት የሚሳተፉ የቀን ሰራተኞች እና የኮሮና ወረርሽኝ



የሰሊጥ ልማት ከማሳ ፅዳት እስከ ረገፋ ድረስ ጉልበት የሚጠይቅ ስራ ነው:: በሰሜን ምዕራብ አትዮጵያ የሰሊጥ ግብርና ከደጋማ ወረዳዎች ለሚመጡ ከ400,000 በላይ ለሆኑ የቀን ሰራተኞች ወቅታዊ የስራ እድል እየፈጠረ የሚገኝ ዘርፍ ነው:: በተለይ ባለሃብት አረሶአደሮች አብዛኛውን ለግብርና ልማት የሚያስፈልጋቸውን ጉልበት የሚያገኙት እነዚህን ሰራተኞች በመጠቀም ነው፡፡ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶአደሮችም በአብዛኛው የቤተሰብ ጉልበት ቢጠቀሙም ተጨማሪ የቀን ሰራተኛ ጉልበት ያስፈልጋቸዋል:: ከዚህ ቀደም በነበሩ ዓመታት አንጻራዊ የቀን ሰራተኛ አቅርቦት እና ተያያዥ ችግሮች በሰሊጥ ልማት ላይ ተፅዕኖ ሲያሳድሩ ተስተውሏል፡፡ አሁን ላይ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ስርጭቱን ለመቆጣጠር መንግስት እየወሰደ ያለው እርምጃ በቀን ሰራተኞች እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ቀላል እንደማይሆን ይጠበቃል::

የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የኮሮና ቫይረስ ስርጭት በዚህ ከቀጠለ የትራንስፖርት አገልግሎት ውስንነት ስለሚኖር የቀን ሰራተኞች እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም የግብርና ግብዓት ስርጭት በተገቢው መንገድ እንዳይፈጸም ሊፈጠር የሚችለውን ተግዳሮት በመገንዘብ የተለያዩ የቅድመ ጥንቃቄ ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ቢሮው በክልሉ ባሉ ዞኖች ወረርሽኙ በአጠቃላይ የግብርና እንቅስቃሴ ላይ ሊያመጣ የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ የተለያዩ ኮሚቴዎችን በማዋቀር ወደየ ዞኖቹ አሰማርቷል::

የምዕራብ ጎንደር ዞን ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በዞኑ ስር ባሉ ወረዳዎች የቀን ሰራተኞች አቅርቦት ላይ ሊፈጥር የሚችለውን ጫና ምን ይመስላል የሚለውን በመዳሰስ ችግሩን ለመቀነስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተወያየ ይገኛል:: የመምሪያ ሃላፊው አቶ ምርኩዝ ዘመነ ስለ ችግሩ ሲገልጹ ሰሊጥ በሚለማበት አካባቢ የማሳ ጽዳት እና የመሳሰሉት ተግባራት የሚከናወኑበት ወቅት ቢሆንም በሰራተኛ እጥረት ምክንያት በአብዛኛው የባለሃብት ማሳዎች እነዚህ ተግባራት ብዙም ሲከወኑ አይታዩም፡፡ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶአደሮች የቤተሰብ ጉልበት በመጠቀም በዚህ ወቀት የሚተገበሩ የግብርና ስራዎችን እያከናወኑ ቢሆንም እነርሱም ጋር ተጽዕኖው በግልጽ ይስተዋላል::

አቶ ምርኩዝ ችግሩን ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አርሶአደሮች የቤተሰብ ጉልበትን አሟጠው እንዲጠቀሙ፣ በደቦ/ወንፈል በመተጋገዝ ስራዎችን እንዲሰሩ፣ አሁን ላይ በአብዛኛው ቦታ ትምህርት ስለተዘጋ በየአካባቢው የሚገኙ ተማሪዎች በግብርና ስራው ላይ እንዲሳተፉ ማስተባበር እንደሚገባ ገልጸዋል:: አያይዘውም ብዛት ያላቸው የቀን ሰራተኞች ሱዳን የሚገኙ ሲሆን እስካሁን 400 የሚሆኑ የቀን ሰራተኞች ተመልሰው በጊዜያዊ ማቆያ ይገኛሉ ብለዋል፡፡::

የቀን ሰራተኞች ስራ ፍለጋ ከቦታ ቦታ እንዲሁም ከማሳ ማሳ ሲንቀሳቀሱ በአብዛኛው በቡድን በመሆን ነው:: በየማሳው ያሉ ካምፖች እና መጠለያዎች በቂ ባለመሆናቸው እና ከፍተኛ የጥራት ችግር ያለባቸው በመሆናቸው የቀን ሰራተኞች ለችግር ሲጋለጡ ይስተዋላል:: አሁን ካለው ወቅታዊ ወረርሽኝ አንፃር ከዚህ ቀደም በነበረው መልኩ የቀን ሰራተኞች መንቀሳቀስ እና በመጠለያዎች መስፈር ችግሩን የበለጠ ስለሚያባብሰው ሁሉም ባለድርሻ አካላት የድርሻቸውን በመወጣት ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ከወዲሁ መከላከል ይገባቸዋል:: ባለሃብት አርሶአደሮች የቀን ሰራተኞች ማቆያዎች ሰራተኞችን ከኮሮና ቫይረስት ስርጭት ለመከላከል በሚያስችል መልኩ ማደራጀት ይገባቸዋል::

ቤኔፊት ኤስቢኤን የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት የቀን ሰራተኞች እጥረት እንዳይከሰት እና የቀን ሰራተኞች ከቦታ ወደ ቦታ ሲንቀሳቀሱ እራሳቸውን ከኮሮና ቫይረስ መከላከል እንዲችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ መልዕክቶችን በፕሮግራሙ ማህበራዊ ትስስር ገጾች እና ድረ-ገጽ እየሰጠ ይገኛል:: መልዕክቱን የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሬድዮ እና በቴሌቪዥን ተመሳሳይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት እና ለማሰራጨት በዝግጅት ላይ ይገኛል::